# የተቃዋሚዎች ችግር

# ከፀረ ዴሞክራሲያዊነታቸው የሚመነጭ ነው

የሃገራችን ተቃዋሚዎች በተለይም ቅንጅትና ህብረት አካሄዳቸው ላይ የሚታየው ችግር ከፓርቲዎቹ ፀረ ዴሞክራሲያዊ ተፈጥሮ የሚመነጭ መሆኑን አንድ ከፍተኛ የኢህአዴግ አመራር ገለፁ።

የኢህአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል አቶ ተሰማ ገ/ህይወት በተለይ ለጋዜጣችን በሰጡት መግለጫ ተቃዋሚዎች ከምርጫ ሳጥን በሚገኝ የህዝብ ውሳኔ ለመገዛት ዝግጁ አለመሆናቸውም ሆነ ህገ መንግስቱን በህገወጥና በአመፅ በመናድ ስልጣን ለመያዝ የሚያደርጉት ጥረት ከፀረ ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካዊ ተፈጥሯቸው የሚመነጭ መሆኑን ገልፀዋል።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች በምርጫው ተወዳድረን እናሸንፋለን የሚል እምነት ያልነበራቸውና ህገ መንግስታዊ ስርአቱም ያልተዋጠላቸው በመሆኑ ወደምርጫው የገቡት ምርጫውን ለህገወጥ አመፃዊና ፀረ ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴያቸው በመሳሪያነት ለመጠቀም መሆኑን አቶ ተሰማ አብራር ተዋል። አያይዘውም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ህገወጥና አመፃዊ አካሄድ መላው ህዝባችን ለተያያዘው የሰላም፣ የዴሞክራሲ፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ግንባታ አደጋን እንጂ ፋይዳን የማያመጣ ነው ብለዋል።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎች ከፀረ ዴሞክራሲያዊ ተፈጥሯቸው የሚቀዳውን የጥፋትና የውድቀት አካሄድ ማስቆም የሚችሉት ሰፊው ህዝብና መንግስት መሆናቸውን አቶ ተሰማ አስታውሰው ህዝቡ በአንድ በኩል የልማት ስራውን በማካሄድ በተጓዳኝ ደግሞ ሰላሙን የሚያደፈርሱትን እረፉ ሊላቸው እንደሚገባና መንግስትም ህዝ ብን ከጎኑ አድርጎ ህግንና ሰላም የማስከበር ግዴታውን መወጣት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

የተያያዙት የጥፋት ጎዳና ለሃገርና ለህዝብ ብቻ ሳይሆን ለራሳቸውም የማይጠ ቅማቸው መሆኑን አጢነው ሰላማዊና ህጋዊ መንገድን በመምረጥ ህዝቡ የሰጣቸውን ድምፅ ይዘው በስርአት እንደ ህዝብ ወኪልነት በአላማቸው ሊቀጥሉ እንደሚገባም አቶ ተሰማ ገልፀዋል። ጰ